# ፅንፈኝነት ወደ አሸባሪነት የሚደረግ ሽግግር ነው!

**ማርታ ሻንካ**

**12-15-14**

ከታሪክ ድርሳናት እንደምንረዳው እንዲሁም አሁን ካለንበት ተጨባጭ ሃቅ የምንገነዘበው አንድ ዕውነታ አለ። እርሱም ፅንፈኝነት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ቅርፅና ይዘቱን ቀይሮ ወደ ጅምላ ጨራሹ አሸባሪነት ሊለወጥ የሚችል መሆኑን ነው።

ታዲያ ከዚህ ነባራዊ ዕውነታ በመነሳት አክራሪነት የሽብርተኝነት ታናሽ ወንድም ነው ቢባል የሚያስኬድ ይመስለኛል። ምክንያቱም በአንድ ወቅት ፅንፈኛ ወይም አክራሪ የነበረ ቡድን ጥቂት ጊዜያቶችን ብቻ ቆይቶ ወደ ግብረ-ሽበራ ድርጊት የሚሸጋገር መሆኑን ሩቅ ሳንሄድ የአካባቢያችን ሁኔታ በግልፅ ስለሚያስረዳን ነው።

መንግሰት አልባ በነበረችው ሶማሊያ ውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረውና ኋላ ላይም በኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት ድባቅ ተመትቶ የተበታተነው አል-ኢትሃድ አል ኢስላሚያ የተሰኘው አክራሪ ቡድን ፣ ራሱን ወደ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ህብረት የተሰኘ ፅንፈኛ ኃይል ቀይሮ ነበር።

ይህ በኤርትራ መንግስት ድጋፍ ሰጪነትና የጥፋት መዘውር ይሽከረከር የነበረው ቡድንም በመከላከያ ሰራዊታችን ፈርጣማ ክንዶች ከተበታተነ በኋላ ቀሪ ርዝራዦቹን በመያዝ አሁንም በአስመራው ቡድን እየታገዘ "ሃረካት አል-ሽባብ አል-ኢስላሚያ" የተሰኘ ቡድንን በመፍጠር ራሱን የምስራቅ አፍሪካ አሸባሪ አድርጎ ለመሾም ጊዜ አልወሰደበትም–ለዚያውም የዓለም አቀፉ አሸባሪ አል-ቃዒዳ የቀጣናው የሽብር ክንፍ በመሆን።

ታዲያ ይህ የማይካድ ዕውነታ በመግቢያዬ ላይ ያነሳሁትን ከአክራሪነት ወደ ሽብርተኝነት የሚደረግን ሽግግርን ፍንትው አድርጎ የሚያሳየን ነው። እርግጥ እንዲህ ዓይነቱ የጥፋት ሽግግር የሚከናወነው የተለያየ አመለካከት ባላቸው የውጭ ሃይሎች እንዲሁም በአንዲት ሉዓላዊት ሀገር ላይ የራሳቸውን ፍላጎት ለማስፈፀም ለሀገሪቱ

ጥቂት በሃይማኖት ስም ለሚንቀሳቀሱ ባንዳ ዜጎች ምንዳ በመስጠት ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተልዕኳቸውን በኃይል ለመጫን በሚሹ አካላት አማካኝነት የሚካሄድ የፖለቲካ ትግል መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ሆኖም ይህ አስከፊና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ክንዋኔ ይዘቱ ፖለቲካዊ እንጂ ሃይማኖታዊ ባለመሆኑ፣ የማታ ማታ የአንድን ሀገር ዜጎች ወደ ጥፋት ጎዳና እንዲያመሩ ማድረጉ አይቀሬ ነው። ለምን ቢባል፤ የተግባሩ ዓላማና ግብ እፍኝ የማይሞሉ ምንደኞችን ለጥፋት ተግባር እያሰማሩ የሀገርን ሰላምና ፀጥታ በማናጋት የተጀመሩትን የሰላም፣የልማትና የዴሞክራሲ ትሩፋቶችን በማጨለም ከህዝቡ ይሁንታ ውጪ ሃይማኖታዊ መንግሰትን ማቋቋም ስለሆነ ነው።

ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ክንዋኔ ብቅ ጥልም አያለ በሀገራችን ውስጥም መከሰቱ አልቀረም። ከቅርብ ጊዜያችን ትውስታ ብንነሳ እንኳን ከዛሬ አንድ ዓመት በፊት አወሊያ በተሰኘው ትምህርት ቤት ውስጥ ጥቂት የሰለፊ ወሐቢይዝም እምነት ፅንፈኛ አራማጆች ተሰባስበው "የሙስሊሙ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴዎች ነን" በማለት የሁከትን ምዕራፍ "ሀ" ብለው መጀመራቸውን እናስታውሳለን።

ታዲያ እነዚህ ጥቂት ፅንፈኞች የራሳቸውን ፍላጎት ማራመድ በሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች ገንዘብ እየታገሱ ህዝበ ሙስሊሙን ሊያደናግሩት ጥረዋል። በዚህም ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያቀረባቸውን ትክክለኛ ጥያቄዎችን በመጠምዘዝና የራሳቸው አስመስለው ከማቅረብ ባሻገር የፖለቲካ አጀንዳቸው ማራመጃ ለማድረግ ሞክረዋል።

ይሁንና መንግስት ትክክለኛዎቹንና የአብዛኛው ሙስሊሞች ጥያቄዎች የነበሩትን ሃሳቦች ሙሉ በሙሉ ሲመልስ እነዚህ ሃይሎች ወትሮም ፍላጎታቸው ሃይማኖታዊ አይደለምና ሌሎች የሙስሊሙ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በማጎን ለፅንፈኝነት እኩይ ምግባራቸው ተጠቅመውበታል። የሀገራችንን ሰላም ለማደፍረስም ተንቀሳቅሰዋል።

ዳሩ ግን ህግና ስርዓትን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት የሀገራችን ዴሞክራሲያዊ መንግስት የእነዚህን ፅንፈኞች ተግባር በከፍተኛ ትዕግስት ሲከታተል ከቆየ በኋላ በህጉ መሰረት የማንኛውም ዜጋ መብት ሳይጓደል ከስር መሰረቱ በማጥራት ተጠርጣሪ

ጥፋተኞችን ህግ ፊት አቅርቧቸዋል። ጉዳያቸውም ባለመብት በሆነው ፍርድ ቤት እየታየ ነው።

ይሁንና የየትኛውም ሀገር አክራሪዎች ፍትህንና ርትዕን በትክክለኛው መንገድ ማግኘት ስለማይዋጥላቸው፣ የእኛዎቹም እፍኝ ፅንፈኞች የወሰዱት እርምጃ በደሴ ሸዋ በር መስጊድ ያስተምሩ የነበሩትን ሼህ ኑር ይማምን በዘግናኝ ሁኔታ መግደል ነበር።

ታዲያ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እዚህ ላይ ልብ የሚልልኝ ጉዳይ ይኖራል። ይኸውም ፅንፈኝነት ቀስ በቀስ እንዴት ንፁሃን ሰዎችን በመግደል ወደ ሽብርተኝነት እንደሚቀየር ሁነኛ ማሳያ መሆኑን ነው።

አንዳንድ ግለሰቦች ግን ይህን ዕውነታ ወደ ጎን በማለት ሰዎች ሃይማኖታቸውን ስለተከተሉ ብቻ እየተጠየቁ መሆናቸውን ይናገራሉ። ይህ ፍፁም የተሳሳተ አባባል ነው። እንደሚታወቀው የሀገራችን ሕዝቦች ብዝሃነትን የማይቀበሉ ሰርዓቶችን በመገርሰስ በምትኩ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነፃነት፣ እኩልነትና አንድነት የሚያረጋግጥ ስርዓት ከተከተሉ እነሆ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ አስቆጥረናል፡፡

የሀገራችን ዜጎች በሚከተሉት እምነት አስተምህሮ ምክንያት ለእስርና ለቅጣት የሚዳረጉበት ስርዓት አክትሟል፡፡ የሀገራችን ሕዝቦች ብዝሃነትን የማይቀበል እንዲሁም ዕውቅናና ዋስትና የማይሰጥ ስርዓትን የሚሸከሙበት ትክሻ ከእንግዲህ አይኖርም፡፡

በፅንፈኝነትና በአሸባሪነት ድርጊት ተጠርጥረው የሚጠየቁ ግለሰቦችን ለሃይማኖታችን ስለታገሉ ታስረዋል የሚለው አቀራረብ የሚመነጨው ከራሳቸው ከአክራሪዎችና ከአሸባሪዎች ነው፡፡

አክራሪና አሸባሪ ኃይሎች ሃይማኖተኛ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ከሕገ-መንግስታችን ጋር የማይታረቅ ቅራኔ ያላቸው በቅዱሳን መጻሕፍትም ጭምር የተወገዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይሎች መቼውንም ቢሆን ለሃይማኖት ነፃነትና እኩልነት ሊታገሉ አይችሉም፡፡ በተቀራኒው ደግሞ የፅንፈኛና የሽብርተኛ አካል ዋነኛ አመለካከትና ተግባር የሃይማኖቶች ነፃነት፣ እኩልነትና አብሮነትን በመጨፍለቅ በግድ በአንድ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ሕዝቡንና መንግስታዊ ስርዓቱን መቆጣጠር ነው፡፡

ስለሆነም ጽንፈኝነት ለማደናገሪያ እንደሚያቀርቡት ለሃይማኖት ነፃነትና እኩልነት የሚታገል ሳይሆን፣ ከእኔ አስተምህሮ ወጣ ያለ ነው የሚለውንና  ሌላውንም ሃይማኖት ለመጨፍለቅ አገር አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና ዓለም አቀፍ ትስስርና መረብ በመዘርጋት የሚንቀሳቀስ ርዕዮተ ዓላማዊ ጉዞ ነው፡፡

በጥቅሉ ፅንፈኝነት ለሃይማኖቶች ህልውና ጥብቅና ሊቆም የማይችል ሃይማኖታዊ ገጽታ የሌለው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የሚጠየቁ ግለሰቦች ቢኖሩ የሚጠየቁበት ጉዳይ ሃይማኖታዊ ሳይሆን የጽንፈኝነት ወይም ከፍ ብሎ በሚከተለው የአሸባሪነት ብሎም ፀረ-ዴሞክራሲ ድርጊት ብቻ ነው፡፡

በሃይማኖታችን ምክንያት በእስር የሚገኙ ግለሰቦች ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ ይፈቱልን የሚለው ማደናገሪያ በሁለት ገጽታው ማየት ጉዳዩን ግልጽ ያደርገዋል፡፡ አንደኛው ማብራሪያ በሚከተሉት እምነት ምክንያት የሚታሰሩ ዜጎች በኢፌዴሪ ስርዓት የሉም፡፡

ተደጋግሞ እንደተገለፀው ጽንፈኝነት ወይም አሸባሪነት ሃይማኖት አለመሆኑን መንግሥትም ሕዝባችንም ጠንቅቀን የምናውቀው ጉዳይ ነው፡፡ ሕገ-መንግስታችን የእምነት ነፃነትና እኩልነት እውቅናና ዋስትና ሰጥቶ ባለፉት 20 ዓመታት በተጨባጭ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም በሃይማኖታችን ምክንያት የታሰሩ የሚለው ማደናገሪያ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ሁለተኛው ጉዳይ አለቅደመ-ሁኔታ ይፈቱልን የሚለው ሲሆን የተጠያቂነትንና የህግ የበላይነት ስርዓት የሚያፈርስና አገራዊ ሰርዓት-አልበኝነትን የሚጋብዝ  አመለካከት ነው፡፡

በሕገ-መግስታችን ሁሉም ዜጎች ማንኛቸውም ልዩነት ሳይደረግባቸው በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለውን መርህም በአደባባይ የሚጥስ  አካሄድ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ የመብት ጥሰቶችን በግላጭ የሚያስተናግድና የሕግ የበላይነትን በገሐድ የሚንድ አካሔድ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡

ታዲያ ፅንፈኛው ኃይል የሕግ የበላይነትን የሚጥሱ ድርጊቶችን ከፈጸመ በኋላ በሕግ ስርዓት እንዳይጠየቅ በሃይማኖት ሽፋን ሕዝቡን ቀስቅሶ ፍትሕ በአገራችን እንዳይሰፍን ለማድረግ የማደናገር ስራውን “ለሃይማኖታችን ብዬ ነው” በማለት ማስቀጠል ይፈልጋል፡፡ በጕዳና ላይ ሁከትና ብጥብጥ ፍትሕ እንዳይከበር፣ የሕግ የበላይነት ተግባራዊ እንዳይደረግ ተጠያቂነት እንዳይኖር ሕዝብን ማደናገር ይፈልጋል፡፡

ፍርድ ቤቶችን በማጣበብና በማደናገር የፍትሕ ሥርዓቱን ለማዛባት መሞከር ዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል ናቸው የሚለው ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ የሚጥስ ነው፡፡ መለመድ የሌለበት አደገኛ አመለካከትና ድርጊት ነው፡፡ ወንጀልን የሚያበረታታ አካሔድ እንደመሆኑ መጠን በአገራችን ሕግ የሚያስጠይቅ ጭምርም ነው፡፡

በሌላ በኩል በሕግ ጥላ ስር የሚገኙ ዜጎች በተጠረጠሩበት ወንጀል ራሳቸውን መከላከል ሕገ-መንግስታዊ መብታቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህን መብታቸውን ተጠቅመው የሚያደርጉትን የሕግ ክርክር በተለየ ሁኔታ ጫና ለማሳደር መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ለመገመት አያስቸግርም፡፡

በተሳሳተ ግምት በጕዳና ላይ ጥያቄና በማኅበራዊ ድረ-ገጽ ጋጋታ የሕግ የበላይነት ሂደት ይስተጓጐላል የሚል አመለካከት የተረጋጋ የክስ ሒደትን የማደናቀፍ ውጤትም ሊኖረው ይችላል፡፡ ይኽም ተመልሶ ተጠርጣሪዎችን ሊጐዳ እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም፡፡

በመሆኑም “በሃይማኖት ምክንያት ይታሰራሉ” የሚለውም ይሁን በተለየ ጫና ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ ይፈቱ የሚለው አካሄድ ፅንፈኛው ኃይል በሃይማኖታዊ ይሁንታ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ሽፍኖ ለመሸጋገር የሚፈጽመው ማደናገሪያ ስለሆነ ሕዝባችን በንቃት ተከታትሎ ድርጊቱን መመከት ይጠበቅበታል፡፡

በተለይም አንዳንድ የአቋራጭ የፖለቲካ ስልጣን ፈላጊዎች ይህንን አጀንዳ በተለያዩ መፈክሮች- “ድምጻችን ይሰማ፤ የታሰሩ ይፈቱ፣ መንግስት በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ…”ወዘተ. እያሉ የማስተጋባታቸው ምስጥር በሃይማኖት ሽፋን ድብቅ የፖለቲካ ፍላጐታቸውን ለማሳካት የተጠቀሙት ስልት እንደሆነ ግልጽ ማሳያ ይመስለኛል፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ እነዚህ አቋራጭ  የፖለቲካ ስልጣን ፈላጊዎች በፕሮግራሞቻቸው ጭምር የሃይማኖት ነፃነትና እኩልነትን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የብዝሃነቶች ህልውና የማይቀበሉ ብሎም የመጨፍለቅ አመለካከት ያላቸው ሃይሎች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እናም ሁሉም ዜጋ ከእነዚህ ሃይሎች ከአሳሳች መፈክሮች በስተጀርባ ያለውን ድብቅ ፍላጐት ማወቅ ያለበት ይመስለኛል–ተግባራቸው ከፅንፈኝነት ወደ አሸባሪነት የሚያመራ መሆኑን።

ለነገሩ እንኳንስ በቀረጸው ህገ - መንግስት ላይ፤ መንግስት በሃይማኖት፣ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ ሳይገቡ  የሁሉም እምነት ተከታዮች የፈለጉትን ዓይነት እምነት ያለ ምንም ጫና በነጻነት የመከተል መብት እንዳላቸው የደነገገ እና በተግባርም የገለጸ መንግስት ቀርቶ፤ ሌሎች ህሊና ያላቸው ወገኖችም ቢሆኑ በየትኛውም ሃይማኖት ላይ ጥቃት የሚከፍቱበት አንዳችም ምክንያት ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ይህ ማለት ግን መንግስት ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ከውጭ ሃይሎች ምንዳ እየተቀበሉ የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታን ለማናጋት የሚጥሩ አክራሪዎችን ዝም ብሎ ይመለከታል ማለት አይደለም፡፡

በሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ጥቂት ግለሰቦች ሰርተው በውጤታቸው ተጠቃሚ መሆን እየቻሉ፣ እምነታቸውን እንደ ሸቀጥ ለውጭ ገበያ በማቅረብ የጽንፈኝነት ተግባርን የሚያከናውኑ ከሆነ፤ ይህን መሰሉን ጸረ - ህገ - መንግስት አካሄዳቸውን እንዳላየ ሆኖ እጁን አጣጥፎ ሊቀመጥ አይችልም፡፡ ህግና ሥርዓትን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት አካል ነውና፡፡

ይሁን እንጂ፤ ቡድኑ ራሱን ለመከላከል ሲል መንግስት በጥቂት ጽንፈኞች ላይ እየወሰደ ያለውን ህጋዊ ተግባር ልክ በእስልምና ሃይማኖት ላይ የተፈጸመ በማስመሰል ለማደናገር ሞክሯል፡፡ ይህ ደግሞ “ምን ያለበት ዝላይ አይችልም” እንዲሉት ዓይነት ይትብሃል በቀጥታ በእስልምና ስም የመነገድ አስፀያፊ ድርጊት ነው፡፡ እርግጥ ፅንፈኛው ቡድን  በሀገራችን ውስጥ መንግስት አንዱን ሃይማኖት በመደገፍ ሌላውን

መንቀፍ የሚችልበት አካሄድ የማይከተል መሆኑን ሊገነዘብ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም ይህን መሰሉ ተግባር የእያንዳንዱ ሃይማኖት ተከታዮችና ተቋሞቻቸው ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡

ታዲያ ፅንፈኛው ቡድን ይህን ሃቅ ወደ ጎን በማለት ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ ሲል የሌለ ድርጊትን በማንቆለጳጰስ የመንግስትን ሰናይ ምግባሮች ለማጠልሸት መሞከሩ ሚዛን የሚደፋ አለመሆኑን መረዳት ያለበት ይመስልኛል።

አክራሪው ቡድን ማስረጃው ምን እንደሆነ ባይታወቅም፤ “መጪዋ ኢትዮጵያ የሙስሊሞች የጭቃ ውስጥ እሾህ እንድትሆን ይፈለጋል፣ ነባሩ እስልምና መብቱን የማይጠይቅ ነው እንዲሁም ተማሪዎችና የመንግስት ሰራተኞች ትምህርትንና ስራን ያስተጓጉላል በሚል በረመዳን ወቅት እንዳይፆሙ ሊደረጉ ይችላሉ።…” የሚሉ እጅግ አሳፋሪና በምናብ የተቀነባበሩ ቅጥፈቶችን ያነበንባል።

ግና ‘ይህ እሳቤ እውነት እኛ በምንገኝባት ኢትዮጵያ ውስጥ አለን?’ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል። እስቲ ይህን ጥያቄ ይዘን ወደ ገሃዱ ዓለም ዕውነታ እንመለስ። እንደሚታወቀው የየትኛውም ሀገር መንግስት የሚመራው ሀገር ለዜጎቹ መጪው ጊዜ ብሩህ እንዲሆን የመሻቱ ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም።

ሆኖም ይህን ዕውን ለማድረግ ሀገሪቱ ለዚህኛው ሃይማኖት ተከታይ የተመቸች፣ ለዚያኛው ደግሞ የምትጎረብጥ እንድትሆን በማሰብ መፈፀም አይቻልም። ምክንያቱም ሀገሪቱ በልማት በልፅጋ መጪውን ጊዜ ለዜጎች ብሩህ ማድረግ የሚቻለው አጠቃላይ ህዝቡን ከዳር እስከ ዳር በማነቃነቅ በየደረጃው በልማቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን እንጂ፤ ፅንፈኛው ቡድን ለማደናገር እንደሚሞክረው የዕድገት ሃይል የሆነውን ህዝብ በሃይማኖት በመነጣጠል አይደለም። ለነገሩ የኢትዮጵያ መንግስትም ይሁን ገዥው ፓርቲ ከአመጣጣቸው ጀምሮ ህዝብን እንደ ህዝብ በማክበር ተግባራቸውን በህዝቡ ጉያ ውስጥ ሆነው ሲከውኑ የመጡ ናቸው።

ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ግን አንዳንድ ሰዎች የአክራሪነት ተግባር መኖሩን እንኳን ለመቀበል ሲያዳግታቸው ይስተዋላል። ሁላችንም እንደምናውቀው ግን ጽንፈኝነት ብሎም

አሸባሪነት የአገራችን፣ የአህጉራችንና የዓለም አቀፍ ስጋት ሆኖ የብዙ ሰላማዊ ዜጐችን ህይወት በሚቀጥፍበትና የንብረት ውድመት እያስከተለ ባለበት ነባራዊ ሁኔታ ላይ በምንገኝበት ወቅት መንግስት ይህንን ያመጣው ለፖለቲካ ፍጆታ ነው የሚለው አቀራረብ የግለሰቦቹንና የቡድኖችን ማንነት ከምንም በላይ በገሃድ የሚያሳይ ነው፡፡

ፅንፈኝነት በአገራችን የለም እያሉ መረባቸውን ለመዘርጋት በቂ ጊዜ እንዲያገኙና ከቁጥጥር በላይ ሆነው ሰላማችንና ልማታችንን በማወክ ህልውናችንን ለመፈታተን የሚያቀርቡት ማደናገሪያ ነው፡፡ ከጎረቤት ሀገሮች ጀምሮ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮች የሰው ሕይወት እንደቅጠል ሲረግፍ እያዩ አላየንም ይላሉ፡፡

በእስያ፣ በአውሮፓ አሜሪካ ወዘተ በየወቅቱ የሚፈጠረውን ቀውስና እልቂት በጆሯቸው እየሰሙ አላዳመጥንም ማለታቸው የተለመደ ነው፡፡ በሀገራችን የሃይማኖት ነጻነትን፣ እኩልነትንና መንግሥትና ሃይማኖትን የሚለያየውን ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ ሲጣስ እያዩና እየሰሙ ይህንን ጉዳይ አንናገርም ይላሉ፡፡

በመሆኑም ድብቅ ፍላጎታቸውን ለማሣካት ሲሉ እውነታውን “አናይም፣ አንሰማም፣ አንናገርም” በሚል ሀገራዊ ክሕደት ይፈጽማሉ፡፡በመጀመሪያ ለህዝባችን ግልጽ የምናደርገው ጉዳይ መንግስት ፅንፈኝነትን የሚፈርጀው ከየትኛውም ሃይማኖት ተነስቶ እንዳልሆነ መታወቅ መቻል አለበት፡፡

ለዚህ ምንያቱ ደግሞ ሁሉም ሃይማኖቶችና እምነቶች የጽንፈኝነት ምንጭ ስላልሆኑ ነው፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ መንግስት ጽንፈኝነትንና አሸባሪነትን የሚፈርጀው ከሕገ-መንግስታችን ከተቀመጡ ሶስቱ የሃይማኖትና እምነት ነፃነት ድንጋጌ መርሆዎች ተነስቶ ነው፡፡ አንደኛው የሃይማኖትና የእምነት ነፃነትን የሚያትተው የህገ መንግስቱ አንቀፅ 27 ነው።

እንደሚታወቀው የእኔን ሃይማኖት ካልተከተልክ በስተቀር አማኝ አይደለህም በሚል ማስፈራራትና አካላዊ ጥቃት ማድረስ፣ ግድያ መፈፀም፣ የእምነት ተቋማትን ማፍረስና ማቃጠል፣ መቃብሮችን ማውደም፣ የሌላውን ሃይማኖት ማንቋሸሽ እና ማብጠልጠል፣

ዜጎች በያዙት ሃይማኖት ምክንያት ማሸማቀቅ፣ በሀይል ሀይማኖታቸውንና እምነታቸውን ለማስቀየር መንቀሳቀስ… ወዘተ. በሀገራችን የተከሰቱ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ታዲያ ይህን ነባራዊ ክስተት የለም በሚል ማከራከሪያ የሚያቀርቡ አካላት ሲኖሩ ራሳቸው ይህንን እኩይ ድርጊት የፈጸሙ፤ የሚደግፉና የተባበሩ ብቻ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የሃይማኖትና የእምነት እኩልነትን የሚገልፀው የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 25 ነው። እንደሚታወቀው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት የሃይማኖታችንን ክብር፣ ሞገስ፣ ታሪክና ጥቅም ቀንሷል፣ ሀገሪቱ የአንድ ሃይማኖት አገር እንጂ ሌሎችን አይመለከታቸውም፣ ከኛ ሃይማኖት በስተቀር ሌሎች አገራቸው ሌላ በመሆኑ እኩል እውቅና ሊሰጥ አይገባም፣ የአማኝ ቁጥር ለማነጻጸር የመሞከር የተሳሳተ አመለካከት፣ አንዳንድ የመልካም አስተዳደር ግድፈቶች በመንግስት መዋቅራችን ሲፈጠሩም አሁንም ሃይማኖቶች እኩል አይደሉም…ወዘተ. ብሎ በማደናገር የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች አሉ።

በተጨባጭ ግን የእነዚህ ወገኖች እሳቤ በሕገ-መንግስት እውቅና ያገኘውን የሃይማኖቶች እኩልነት የሚንድ ተግባር ነው። ታዲያ ይህን አመለካከት መንግስት ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ልንታገለው ይገባናል። እሳቤው ፀረ-ዴሞክራሲና ፅንፈኛ የሆነ አስተሳሰብና ተግባር ነው፡፡

ታዲያ ይህን አመለካከትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ የለም በሚል መከራከሪያ የሚያቀርቡ አካላት ራሳቸው ዋነኛዎቹ የፀረ-ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ተሸካሚና ድርጊት ፈጻሚዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ዳሩ ግን የማንኛውም እምነት ተከታይ ያለማንም አስገዳጅነት በመረጠው ሃይማኖት እንዲመራ፣ ሃይማኖታዊ ግዴታውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲፈጸም እንዲሁም መንግስትና ሃይማኖት ብሎም ሃይማኖትና የትምህርት ተቋማት ተነጣጥለው

ተግባራቸውን እንዲከውኑ በማድረግ ረገድ ህገ - መንግስታዊ ድንጋጌው ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በተግባር እንዲተረጎም አድርጓል፡፡

የጨለማው ተጓዦች ለብሶት ማራገቢያነት በሌለ ተጨባጭ ምህዳር የሚያነሷቸውና ባለፉት ስርዓቶች የሚከተሏቸው የሃይማኖት ጭቆናዎች እና የፍትህ መጓደሎች እንዲወገዱ በማድረግ ረገድም ግዙፍ ቦታ የሚሰጠው ርምጃ በመንግስት በኩል ተወስዷል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። ባለፉት 23 ዓመታት ሁሉም ሃይማኖቶች አምልኮአቸውን የሚፈጽሙባቸው የእምነት ቦታዎች ከመስፋፋታቸው በተጨማሪ፤ የመቻቻል ባህላችን ማሳያ የሆኑት የሃይማኖት በዓላት ክብደት በሚሰጣቸው ሁኔታ እንዲከበሩ አስፈላጊ የሚባሉ ጉዳዮች ተመቻችተዋል፡፡

እነዚህ የሃይማኖትት እኩልነትን በተግባር ለመተርጎም የተከናወኑ ሃቆች ሀገራችን ውስጥ በማንኛውም እምነት ተከታይ ዘንድ ነባሩን የመቻቻል ባህል ይበልጥ ያሰፉና ያረጋገጡ እንጂ፤ ለአንድ ሃይማኖት የውስጥ ግጭት በር የሚከፍቱ ክንዋኔዎች አለመሆናቸውን መገንዘብ ያሻል፡፡

በመሆኑም በዚህ የመቻቻልና ተፈቃቅሮ የመኖር ነባራዊ ምህዳር ውስጥ የጽንፈኞቹ የአመጽ ድቤ መቺነት የትም የሚያደርስ ሊሆን አይችልም፡፡ በእኔ እምነት፣ ይህን የሀገራችንን የመቻቻል ሃይማኖታዊ ባህል ለማጉደፍ በኦርቶዶክስም ይሁን በእስልምና እምነቶች ውስጥ ሰርገው እየገቡ የሌለ አጀንዳን እያነሱ ሁከትና ብጥብጥ ለመቀስቀስ የሚሞክሩ ወገኖች ተቋማቱን የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ማድረግ የሚፈልጉ ናቸው፡፡

እነዚህ ኃይሎች በሀገር ውስጥ የከሰረ የፖለቲካ አጀንዳን ብቻ የሚያራምዱ አይደሉም፡፡ በጎረቤት ሀገር ካሉ አክራሪዎች ጋርም ንክኪ ያላቸውም መሆኑን ጠቋሚ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሶማሊያ ፅንፈኝነትን የሚያራምዱ አክራሪዎች በአቋም ደረጃ አፍሪካን ከምስራቅ እስከ

ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ ዋልታዎቿ ድረስ በእስልምና ሃይማኖት እናጠምቃታለን እያሉ ሲያሟርቱ ነበር።

ታዲያ ይህ የትስስሩ አንድ አመላካች ጉዳይ ሆኖ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ እናም በሀገራችን በሃይማኖት ሽፋን ግጭትን የመቀስቀስ ፍላጎት አባዜ በሌላ ገጽታው የራሳቸው አጀንዳ ያላቸው የውጭ አክራሪዎች እጅ ያለበት መሆኑ ሁነኛ አስረጅ ነው፡፡

እነዚህ ሃይሎች ሰው በሰብዕናው እኩል ከሆነ የሚከተለው የራሱ አመለካከትና እኩልነት መከበር ሲገባው ሐይማኖቶችን በሁለተኛና በሶስተኛ ደረጃ ፈርጀው የሚንቀሳቀሱም ጭምር ናቸው፡፡ ምልከታቸው ሕዝቦች ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚክድና ሃይማኖት ተከታዩ ህብረተሰብ በከፍተኛ የጋራ መስተጋብር በሠላም አብሮ የኖረ መሆኑን የሚዘነጋ በመሆኑ ሊወገዝ ይገባል፡፡

መንግስት ፅንፈኝነትና አሸባሪነትን የሚፈርጅበት ሶስተኛው ምክንያት በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 11 ላይ የተጠቀሰውን የሃይማኖትንና የመንግስትን መለያየት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው። መንግስታዊ ሀይማኖት እንደማይኖርና መንግስትም በሃይማኖት ጣልቃ እንደማይገባ በሕገ-መንግስታችን በማያሻማ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ከዚህ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ተነስተን መንግስታዊ

ሃይማኖት ወይም ሃይማኖታዊ መንግስት ለመመስረት የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በፅንፈኝነት የሚፈረጅ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አሁንም እንዳለፈው ዘመን “መንግሥታዊ ሃይማኖትን ዕውን እናደርጋለን” በሚል የሚንቀሳቀሱ መኖራቸው፣ ሌሎች ደግሞ መንግስታዊ ሃይማኖት የመመስረት ጊዜው የኛ ነው ብለው የሚንቀሳቀሱ አካላት ተፈጥረዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ አሁንም ያው የድሮው ነው የተለወጠ ነገር የለም ብለው የሚንቀሳቀሱና መንግስትና ሃይማኖት እንዳልተለያየ አድርገው የሚሰብኩ መኖራቸው የአክራሪነትና ጽንፈኝነት ጉልህ ማሳያ ነው፡፡

እነዚህ አመለካከቶች በሌላ መልኩ ሲታዩ ከትምክህትና ከጠባብነት የሚመነጩ እንዲሁም ሀገርንና ሕዝብን የሚንዱ አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ በሃይማኖት

ተቋማት ሥር በተደራጁ የወጣት ማህበራትን እንደምሽግ የሚጠቀሙ ግለሰቦችና ቡድኖች በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ አመለካከትና ተግባር በጊዜ ሂደት ወደ አሸባሪነት የሚሸጋገር እንደሆነም በሀገራችንም ጭምር እያየነው ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባ ጉዳይ ሃይማኖት በራሱ የሰላም ምንጭ እንጂ የአክራሪነትና ፅንፈኝነት ባህሪ የለውም፡፡

የሃይማኖት ተከታዮችም የዘውትር ጸሎታቸውና ፍላጎታቸው መንግሥታዊ ሃይማኖት ወይም ሐይማኖታዊ መንግሥት መመስረት ሳይሆን ሠላምና ልማት ነው፡፡ ነገር ግን ሃይማኖትን መሳሪያ አድርገው የፖለቲካ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚጥሩ እንዳሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። በሀገራችንም በዚህ መንገድ የብዙ ሰዎች ህይወት እንደጠፉ፣ አካል እንደጎደለ፣ መስጊዶችና ቤተክርስቲያኖች እንደተቃጠሉ የሚታወቅ ዕውነታ ነው፡፡

በመሆኑም መንግስት ፅንፈኝነትንና ሽብርተኝነትን ሲፈርጅ እነዚህን ሶስቱን ሕገ-መንግስታዊ ሃይማኖት ነክ የዴሞክራሲ መርሆዎችን ከመፃረርና ካለመፃረር አንፃር መዝኖ ነው።

እርግጥ ፅንፈኝነት የሌላውን ህልውና የማይቀበልና፣ አብሮ በሰላም መኖርን እንደ ስጋት የሚወስድ፣ ብዝሃነትን የማይቀበል፣ ተከባብሮና ተደማምጦ መኖር የሚባል ነገር የማያስተናግድ አስተሳሰብና ተግባር ነው፡፡

ታዲያ እነዚህን ሦስቱን ሕገ-መንግስታዊ መርሆዎች በገሐድ እየጣሱ በሌላ በኩል በአገራችን አክራሪነት/ጽንፈኝነት የለም፣ ለፖለቲካ ፍጆታ መንግስት የፈጠረው አጀንዳ ነው የሚሉ አካላት ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ የሆነውን ድርጊቶቻቸውን ለመደበቅ የሚያደርጉት ማደናገሪያ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ እነዚህ ሃይሎች ንጹሐን ዜጎችን በፅንፈኝነት ተግባር የመመልመልና የማስፋፋት እቅዳቸውን ለማሣካት መንግሥትንና ሕዝባችን የማዘናጋትና ጊዜ የመግዛት ዘመቻና ማደናገሪያ እንደሆነ

በግልጽ ሊያዝ የሚገባ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ጽንፈኝነትን ቅዱሳን መጻሕፍትና የሃይማኖት አባቶችም ከአስተምህሮዎቻቸው እየተነሱ የሚያወግዙት አመለካከትና ተግባር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ፅንፈኞች ግን ከዚህ ቀኖና ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሃይማኖትን ተጠልለው ይህን ተግባር ለመፈፀም ይሞክራሉ።

ያም ሆነ ይህ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ፅንፈኝነት ተግባሩና አስተሳሰቡ እየቀነሰ የሄደ ቢሆንም፤ የሀገራችን ተጨባጭ ችግርና ወቅታዊ ስጋት መሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱ ዜጋ ይህን ወደ ሽብርተኝነት ከፍ ሊል የሚችልን እኩይ ተግባር ለመከላከል መረባረብ ይኖርበታል፡፡